መስከረም 15/2015

**የትግራይ ህዝብ ቀዳሚ ጥያቄው ምንድነው? መገንጠል ወይንስ ህልውናውን በኢትዮጵያ ውስጥ ማስከበር?**

W. YILMA

# መግቢያ

የትግራይ ህዝብ እንድማንኛውም ህዝብ ለኢትዮጵያ ሃገረመንግስትና ግንባታ ከፍተኛውን ድርሻ አበርክቷል። ሆኖም ይህ ማህበረሰባዊ ተሳትፎ የነበረውን የዘመናት ትግል ለራሱ ማህበረሰብ ዘለቄታ ያለው ሰላምን አላስገኘለትም። በዚህም ምክንያት የራሱን ሶሻል ካፒታል ተጠቅሞ ማህበረሰቡን ሊጠቅሙ የሚችሉ የኢኮኖሚ፡ የባህል፡ የስነጥበብ ቋንቋና የሥርዓተ ትምህርት እድገት ለማምጣት አላስቻሉትም። ይህም አልበቃ ብሎ ሌሎች እሱ በታሪክ ሰሪነቱ የሚገባውን ክብርና ቦታ ከመስጠት ይልቅ በራሳቸው ወይንም ከሌላ የውጭ ባዕድ ሃይል ጋር በመመሳጠር የትግራይን ህዝብ በማንኳሰስ እራሳቸውን የታሪክ ፈጣሪ አድርገው ከመቁጠራቸውም በተጨማሪ ለትግራይና ለሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ዜግነት ሰጪና ከልካይ ሆነው የተገኙበት ግዜ ላይ ደርሰናል። ከዚህም አልፎ በአቢይ አህመድና በኤርትራው ጨካኝና አረመኔ መሪ ፊትአውራሪነት እንዲሁም በአንዳንድ የኢትዮጵያ ብሄር ጽንፈኞች ጋሻ ጃግሬነት አልፎም በአንዳንድ የአረብ ሃገራት እገዛና አይዞህ ባይነት በትግራይ ህዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን መሬቷ አቅፋ በያዘቻቸው የተፈጥሮ ሃብቷ እና በታሪኳ ላይ ሁሉ አቀፍ የሆነ የጥፋት ጦርነት አውጀው በመዝመት ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል በትግራይ ህዝብ ላይ በመፈጸም ላይ ይገኛሉ።

ይህን ግፍ የተመለከተ የትግራይ ህዝብ ወጣት፡ ሽማግሌ፡ ሴት ወንድ የተማረ ያልተማረ ጤነኛ በሽተኛ ሳይል ተጠቂነቱ ባስከተለበት ቁጭት ተነሳስቶ ዱር ቤቴ ብሎ በከተማ የነበረው ጨርቁን ማቁን ሳይል ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጎና ትቶ ምታ ነጋሪት ክተት ሰራዊት ብሎ እጁ ጠብመንጃ ወደመያዝ ተሸጋገረ። በዚህም በጥቂት ጊዜ ውስጥ ተደራጅቶና ሰልጥኖ ዘመናዊ አስተሳሰብ ሳይላበስ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ አስከአፍንጫው የታጠቀውን የአቢይ እና የኢሳያስ መንጋ ሰራዊት የትግራይ ሰራዊት በጥቂት ግዜ በአካሄደው ወታደራዊ ኦፐሬሽን ከአብዛኛው የትግራይ መሬት ጠራርጎ ጥጋቸውን አስያዛቸው።

የዚህ ጽሁፍ አላማ የትግራይን ህዝብ ድል ወይንም በጦርነቱ ምክንያት በትግራይ ህዝብ ላይ የደረሰውንና እየደረስ ያለውን ግፍ ለማውሳት አይደለም። ይህን ላድርግ ብልም የተሰራው ግፍ አሁን ህዝቡ እያየ ካለው መከራ እጅግ የገዘፈ በመሆኑ ጊዜና ቦታ የሚበቃኝ መስሎ አይታየኝም። ስለሆነም ከላይ በጠቀስኩት ርዕስ ላይ በማተኮር ዘለግ ያለ አስተያየት ወደመስጠቱ ልሸጋግር።

## የትግራይ ህዝብ ቀዳሚ ጥያቄው ምንድነው?

ይህንን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ እራስን አንድ እንደፖለቲከኛ አድርጐ በማየት ሳይሆን እራስን በህዝቡ ጫማ ውስጥ ከቶ ማየት ያስፈልጋል።ይህ ሲሆን የትግራይ ህዝብ እንድማንኛውም ህዝብ የሁሉም እድገት መሰረት የሆነውን ሰላም ይፈልጋል።ግን ሰላም እንዴት ይመጣል? ለእኔ ይህ ጥያቄ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁለንተናዊ እውነታዎችን የምገነዘብ ቢሆንም በሀቅ ላይ የተመሰረተ መልስ ለመስጠት እጅግ እቸገራለሁ። ለምን ቢባል አንደኛ የኢትዮጵያ ህዝብ የማውቀው መስሎኝ አለማወቄና አሁን የተረዳሁበት ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ለኔ የሃብሻ ፖለቲካ መነሻው ስለማይታወቅ መድርሻውም አይታወቅም። የሃበሻ ፖለቲካ ሲጀመር ጀምሮ እብዶች ወይንም ተምረው ያልተማሩ ባዶ ጭንቅላቶች ተጣምረወና ተዋህደው ተንኮልና ሴራ አክለውበት በዙ ሳይገባው አጨብጫቢና አዳማቂ መንጋ በማስከተል የሚመሰርቱት መሰረተ አልባ ሥራዓት ይመስለኛል። ለዚህም ነው አንደኛ-ዛሬ የመከነ በውሸት የተሞላ “አውርቶ አደር” ትውልድ ቀፍቃፊ በመሆን ችግር ጠማቂ እንጂ ችግር ፈቺ ትውልድ አልባ የሆነችው። ሁለተኛ- ለተወሰኑ አመታት በአንፃራዊነት ሰላምና የኢኮኖሚ እድገት አግኝተን

የነበረ ቢሆንም የመንግስት ባህሪው የአስተዳደር ዘይቤውና የፖለቲካው አመራሩ በድንብሩ ከመሄድ ውጪ በታቀደና ነጻ የህዝብ ተሳትፎ ያለው አስትዳደር በመመስረት ዘላቂ ሰላምና የኢኮኖሚ እድገትን በሚያመጣ መልኩ ቅርፅ ይዞ መደራጀት አለመቻሉ አሁን ወደደረስንበት ቅጥ አምባሩ የጠፋበት ጊዜ ላይ እንድንደርስ ዳርጐናል። ይህ በመሆኑም ነው እስካሁን ድረስ የችግር አፈታታችን ማህበራዊ መሰረቱ በጦር አሸናፊነትና ተሸናፊነት መንፈስ ብቻ እንዲወሰን መደላደል ያበጀነው። ይህ በመሰረቱ ኋላቀርነት ነው ብቻ ተብሎ የሚታለፍ ሳይሆን በእጅጉም ከሰው ልጅ ፍጡርነት ደረጃ እጅግ ዝቅ የሚያስደርግ ስነምግባር ነው። እኔ አስከማውቀው ድረስ ከአንድ በላይ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው ችግር ከመፍታት ይልቅ ችግር ቀፍቅፈውና ወልደው ተጣልተው የሚለያዩበት አጋጣሚዎች እጅግ የበዙ ናቸው። ታድያ ይህ ከሆነ እንዴት ነው በሺህ በሚቆጠሩ ቅጥ ያጡ ገንዘብና ንዋይ ተከፋዮችና ተሸላሚዎች ብሎም የደሃ ህዝባቸውን ስቃይና ሰቆቃ በማብዛትና ደም በማፍሰስ አልፎም የንፁሃን ህይወት በማጥፋት ህይወታቸውን የሚያለመልሙ የሚመስላቸው የማህበራዊ ሚዲያ ተዋናዮች በሚዘውሩት የጨፍጫፊው የአቢይ መንግስትና ህዝቡን ከመጥፋት በሚከላከለው የትግራይ መንግስት መካከል ሊካሄድ የታሰበው ድርድር ሰላምን ይስገኛል ብለን ተስፋ የምናደርገው? ይህ የግሌ ስጋት በመሰረቱ ሁሉንም ሰላም ወዳድ ወገን ጦርነቱን ካላስቆመ በአእላፍ የሚቆጠሩ ዜጐች ደመከልብ የሚሆኑበትን ሁኔታ መፈጠር መቻሉ ብቻ ሳይሆን የህገሪቷም ሁኔታ ደህንነት ከድጡ ወደ ማጡ ሊሸጋገር ይችላልና ነው። በተለያየ ግዜና ወቅት አዲስ አበባ ካለው መንግስት የሚሰጡት የተምታቱ መግለጫዎች ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው።

አንድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የትግራይ ህዝብ በዚህ ጦርነት አጥቂ ሳይሆን ተጠቂ ነው። ሄዶ ሳይሆን እደጁ መጥተውበት ነው እያጠቁት ያሉት ።መብቱን ፤፡ሃብቱንና ንብረቱን ተነጥቆ የነጠቃችሁኝን መልሱልኝ እያለ ነው አይተዋጋ ያለው። ስለዚህ ምንም እንኳን ትግራይን እያስተዳደረ ካለው የፖለቲካ ቡድን ጋር የፖለቲካና የርዕዮተ አለም መጣጣም ባይኖረኝም የኢትዮጵያ መንግስት ነኝ ከሚለውና ሙሉ መስተዳደሩ በተንኮልና በውሸት ተከሽኖ የተጠነሰሰ ጣኦት አምላኪ ስብስብ ከሆነው አብይ አህመድ ቡድን የትግራይ መንግስት ለሰላም ዋጋ ይሰጣል ብዬ አምናለሁ። ሆኖም ግን ይህን ስል ከስጋት ነጻ ነኝ ማለት አይደለም። ይህንንም በተመለከት ደጋፊ ሃሳቤን ከዚህ ቀጥዬ አቀርባለሁ።

**የታሰበው ድርድር ተሳክቶ ሰላም ያመጣ ይሆን?**

እንደሚታወቀው የጦርነት ግጭትን በሰላም ድርድር ለመፍታት የሚደረግ ጥረት እጅግን አስልቺና ጊዜ የሚውስድ ሂደት ነው። በተለይም ፍጹም ጥላቻ በነገሰበት አንደኛው ተደራዳሪ በሌላኛው ተደራዳሪ ላይ ጥገኛ ከሆነ ድርድሩ በተወሰነ ጊዜ ያልቃል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። በአብይ መንግስትና በትግራይ መካከል የሚደረገው ድርድርም ከዚህ የተለየ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም።ለዚህ ነው የአብይ መንግስት ተንኮልና ሴራ ለማጋለጥ የትግራይ መንግስት ለመደራደሪያነት የሚያቀርባቸው ነጥቦች የሚደራደረውን ወገን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የአደራዳሪዎችንም ቀልብ የሚስብ መሆን አለበት የምለው።ምክንያቱም አደራዳሪዎች ከፍተኛውን ድርሻ የሚኖራቸው መሆኑን ግምት ውስጥ በማግባት በአጭሩ የድርድሩ ነጥቦች ጊዜና ወቅትን የአሁንና የወደፊቱን ግብ የሃይል ሚዛን ብሎም የሩቅና የቅርብ ሀገራትን የሃይል አሰላለፍና ፍላጎትን እንዲሁም የትግራይን ህዝብ የቅደም ተከተል ጥቅሞች ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።መሰመር ያለበት ጉዳይ ግን የድርድሩ ሂደት የጊዜ ገደብ ሊኖረው ይገባል። ምክንያቱም ጊዜ ማራዘም ማለት ለአብይና ኢሳያስ የትግራይን ህዝብ የማጥፋት ፕሮጀክቶቻቸውን ቀጥሉበት እንደማለት ነው። እኔ እንደሚገባኝ ሰው ሆኖ የሰው ባህሪና ፀጋ የተላበሰ ፍጡር ጦርነት የማንኛውም ያለመግባባት ችግር የመፍቻ ቁልፍ ነው ብሎ አያምንም። በይበልጥም አዲስ አበባ ላይ ስልጣን ተቆናጦ ያለው ስብስብ ባህሪ ለተረዳና በሚካሄደው የርስ በርስ ጦርነት የውጭ ጣልቃ ገብነት ጥልቀቱና መጠኑን ለተገነዘባ ሰው እየተካሄድ ያለው ጦርነት መቋጫ ያገኛል ግምት አይኖረውም። ለምን ቢባል፡-

1- በለስ ቀንቶት ስልጣን ላይ ያለው ስብስብ ባህሪያት ከጦርነት ውጪ ሌላ ህዝብ አስተዳደርበታለሁ የሚለው አዕምሮዊ አቅም፤ ፕሮግራምና ራዕይ የሌለው መሆኑ።
2- በትግራይና ሌሎች አካባቢዎች ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆኑ የጦርና የዘር ማጥፋት ወንጀሎች የፈፀሙ አካላት ከተጠያቂነት የማያመልጡ መሆኑን አቢይና የሱ ባለስልጣናት ስለሚያውቁ።
3- የተወሰኑ የሃገር ውስጥ ቡድኖች አንኳን ሰላምን ለመፍጠር ቢጥሩ በጦርነቱ የተሳታፉት የውጭ ኃይላትና እነሱ የገዟቸው ባንዳዎች ድርድሩን ከማደናቀፍ የማይመለሱ መሆኑ
4- ድርድሩ ባጠቃላይ የቡድኖችን ጥቅም አንጂ የህዝብን ዘለቄታዊ ጥቅምና ፍላጐት የሚያስቀድም ነው ተብሎ ስለማይገመት።
5- የጦርነቱ ዋና ተዋናዮች አብይና የኤርትራው ኢሳያስና የሱ ሎሌዎችና ታዛዦች ዋናው አላማቸው የትግራይን ህዝብ ቢቻል በጦርነት ካልሆነ መግቢያ መውጫ አሳጥተው በረሃብ ማጥፋትና ድንበር መግፋት ስለሆነና ይህን እስከሚፈፀሙ ድረስ ጦርነቱን የማቆም ፍላጐት የሌላቸው መሆኑ።

6-በአብይ ደካማ አስተሳሰብ ምክንያት በኢትዮጵያ ለተከሰቱት ዘርፈ ብዙ ቀውሶች ህዝቡ ተቃውሞ እንዳያነሳ ጦርነትን መፈብረክ የዕለት ስራው የሆነ መንግስት ስልጣን ላይ ያለመሆኑ ሊጠቀሱ የሚችሉ ምክንያቶች ሲሆኑ በዚህ ላይ ህዝቡ “ቢጭኑት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ” ሆኖላቸዋል።

**የትግራይ ህዝብ መሰረታዊ ጥያቄ መገንጠል ወይስ ሌላ?**

በትግራይ ህዝብ ላይ ህገወጥና ምክንያት አልባ የሆነ በዚህ ዘመን ያውም በራስ ህዝብ ላይ ይደርሳል ተብሎ የማይታሰብ ግፍና በደል ተፈጽሞበታል። ይህ በመሆኑም አሁን ትግራይን እያስተዳደረ ያለው ፓርቲ እንዲሁም ከህዝብ አብራክ ወጥተው ህዝባቸውን ከተጨማሪ መከራ የታደጉት የትግራይ መከላከያ ሀይላት አልፎም በአብዛኛው በውጭ በሚኖሩ የክልሉ ተወላጆች አሁን አጉልተው እያነሱ ያሉት ጥያቄ ትግራይ የራሷን ሀገረመንግስት መመስረት አለባት የሚል ነው። በአዲስ አበባው መንግስትና እውር ደጋፊዎቹ በትግራይ ህዝብ ላይ የደረሱትንና እየደረሱ ያለውን ወንጀልና በደል ለሚገነዘብ የሰው ባህሪ ያለው ፍጡር የመገንጠል ጥያቄ ከትግራይ መቅረቡን እንደትልቅ ነገር አክብዶ አያየውም። ሆኖም ግን እኔ በግሌ ይህን ጉዳይ በሚመልከት የጠለቀ እውቀትና ምልከታ ኖሮኝ ኢጋዥ መረጃዎችን ከታሪክ ማኅድራት በመርመር፤ በመረዳትና በማጣቀስ የትግራይ ከኢትዮጵያ መገንጠልን ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም በዚህ ወቅት በቂ እውቀትና ዝግጁነት አለኝ ብዬ አላስብም። ምክንያቱም ይህ ጉዳይ (ይህን በሚመለከተ አሁን በስራ ላይ ያለው ህገመንግስት በግልጽ ያስቀመጣቸው የአፈጻጸም ሂደቶች እንዳሉ ሆኖ ) መወሰን ማለት በብዙ ሚሊዮኖች ህዝብ የወደፊት አጣፈንታ ላይ መወሰን ከባድ መስሎ ስለሚሰማኝ ብቻ ሳይሆን አሁን ያለው የኢትዮጵያና የአካባቢው የፖለቲካ፤የጸጥታና የወታደራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ይህ ሲባል ግን በጉዳዩ ላይ አስተያየት ከመስጠት አራሴን አልገታም።

በእኔ እድሜ የተወሰኑ ሀገራት ከአንድ ሀገርነት ወደ ብዙ ሀገርነት ተለውጠው አይቻለሁ። ሆኖም ግን የአንዱ ሀገር ታሪክ ከሌላኛው ጋር ሲነጻጸር ምክንያቶቻቸው የተለያዩ ናቸው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ደቡብ ሱዳን ከሱዳን ተገንጥለው ሀገር ተብዬ መስርተዋል። ዩጐዝላቪያ በእርስ በእርስ ጦርነት ከታመሰችና ከወደመች በኋላ ተፈረካክሳለች በተመሳሳይ መልኩ ያለምንም ጦርነት ሶቪየት ህብረት አስራ አምስት ሀገር ወልዳ ተበታትናለች። ሆኖም ሂጂ ብላ ከለቀቀቻት ዩክሬን ጋር በአሁኑ ሰዓት አውዳሚ ጦርነት እያካሄደች ትገኛለች። በአንጻራዊነት ከዩጎዝላቪያ ከተበታተኑት አዲስ ሀገራት በስተቀር ሌሎች አዲስ የተፈጠሩት ሀገራት በወጣላቸው አምባገነን መሪዎች ወደሚተዳደሩበት ሀገርነት ነው የተለወጡት። አዲስ ሀገር ለፈጠሩለት ህዝብም መልካም አስተዳደር የኢኮኖሚ እድገትና ሰላምን አላስገኙለትም። መታወቅ ያለበት ጉዳይ ከላይ የተጠቀሱት ሀገራት በውስጣቸው የነበረው አለመግባባት ወይንም ጦርነት የግድ ተገንጣጥለው ሀገር እንዲሆኑ የሚገፋፋቸው በቂ ምክንያት አልነበራቸውም። መገንጣጠሉን ለማፋጠን የምዕራባውያን ጥቅሻና ይሁንታ በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ አድርገዋል። የኢትዮጵያን ለየት የሚያደርገው የአዲስ አበባው ዱርዬ መንግስት ሆን ብሎና አቅዶ ከውጭ ጠላቶች ጋር በመመሳጠር የትግራይ ህዝብ ላይ ከዚህ በፊት የእርስ በእርስ ጦርነት ታሪክ ያልዘገበው ግፍና በደል በማድረስ ህዝቡ ከሚወዳትና ከሰራት ሀገሩ የመገንጠልን ጥያቄ እንዲያነሳ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ ነው። እዚህ ላይ ሳለነሳ የማላልፈው ጉዳይ ቢኖር በትክክል የሂትለር ባህሪና የጭካኔ ጥግ እንዲሁም በስሩ የነበሩ የፕሮፓጋንዳ አውታሮች ድርጊትና ስምሪት በምሳሌነት በ 21ኛው ክፍለዘመን ይጠቀስ ቢባል የአሁኗ ኢትዮጵያ ጥሩ ምሳሌ ትሆናለች። ሆኖም በትግራይ ላይ የተሰራው ግፍ ልዩ የሚያደርገው ሂትለርና ግብራአበሮቹ የጭካኔ አባዜያቸውን የተወጡት የራሳቸውን ህዝብ በመጨፍጨፍ ሳይሆን የነሱ ባሉሆኑ ህዝቦች ላይ መሆኑ ነው ። ይህ ብቻ አይደለም ከውጭ ጠላት አገር ጋር ሆኖ የራሱን ህዝብ የወጋና ያስወጋ አሁን በሰልጣን ላይ ያለው አእምሮ አልባው ጠ/ ሚንስትር በአለም ታሪክ የመጀመሪያው ይሆናል። ይህም ሆኖ በኔ ግምት ምዕራባውያን ከዚህ በፊት ለሌሎች የሰጡትን የመገንጠል ይሁንታ አሁን በኢትዮጵያ ላይ የተገብሩታል የሚል የለኝም። ይሄአንዱ ሲሆን ሌላው አሁን ትግራይ ያለችበት ሁለንተናዊ ሁኔታዎች በራሱ አሁን ልንገነዘባቸው ያልቻልናቸው ሌሎች ተጨማሪ ፈታኝ ክስተቶችን ያስከትላል የሚል ምልከታ አለኝ።ከላይ እንደገለጽኩት የአብይ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣበት ቀን ጀምሮ ከአንዳንድ የጽንፈኛ ቡድኖችና ግለሰቦች አልፎም ከኤርትራው አምባገነን መንግስትን በመጠቀም አቅዶና አውጥቶ በትግራይ ህዝብ ላይ ፋሺስታዊ የሆነ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ዘርቷል። በዚህም ጦርነቱ ሲጀመር መሳሪያ በታጠቁ ቡድኖች መካከል ብቻ ሳይሆን መሳሪያ ባልታጠቁ የትግራይ ህዝብ ላይ እንዲሆን አድርጓል። ከዚህም አልፎ ትግራይን በሙሉ ከበባ ውስጥ አስገብቶና መሰረታዊ አገልግሎቶችን አግዶ ህዝቡ እንዲራብና እንዲሞት አድርጓል እያደረገም ይገኛል። ይህ ከበባም በትግራይ ህዝብ ላይ ከፍተኛ የሆነ ማህበረ ኢኮኖሚ አልፎም በህዝቡ ስነልቦና ላይ የሰው ልጅ በሰነድ ሰንዶ ሊያስቀምጣቸው ከሚችለው በላይ ጫና ፈጥረውበታል። ይህ በዚህ ከቀጠለም የዘር ማጥፋቱን ሂደት ያፋጥነዋል።ይህም አብይና የሱ አጋሮች በትግራይ ህዝብ ላይ ያቀዱትንና የወጠኑትን ሁሉ እንዲያሳካላቸው እድል ይሰጣል። ማወቅ ያለብን በሙቶ ሺህ የትግራይ እንስቶች ላይ በወራሪዎች የተፈጸመው አስገድዶ መድፈር በትግራይ ውስጥ የነበሩትን

የማምረቻና የአግልግሎት መስጫ ተቋማት መዝረፍና ጨርሶ ማውደም የህክምና ሰጪ ተቋማትን አንዳልነበሩ ማድረግ የትግራይ ተወላጆችን በያሉበት እየታደኑ ያለልዮነት ማሰር፤ገድሎ ማቃጠልና ወደ ገደል መወርወር ወዘተ... በራሱ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ሳያስፈልገው የዘር ማጥፋቱ ወንጀል አካል ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።

ከላይ በጥቂቱ የተጠቀሱትን ወንጀሎች በአብይ መንግስት መፈጸማቸውን የአለም መንግስታትና አለም አቀፍ ተቋማት ጠንቅቀው ያውቁታል፡ ችግሩ ያለው ወንጀል መፈጸሙን ማመን ወይንም አለማመን ላይ ሳይሆን ጉዳዩ የጂኦ ፖለቲካ ጥቅማቸውን ሳይነካ እንዴት በዳዩንና ተበዳዩን ማግባባት እንችላለን በሚሉ ኃያላን መንግስታት መካከል መግባባት ስለጠፋ ነው። ይህ በመሆኑም የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያ መንግስት ከደረሰበት ወንጀል በተጨማሪ እንደአለም ማህበረሰብ አባልነቱ የሚገባውን ድጋፍና እገዛ ከነዚህ አካላት አላገኘም። ይህ ደግሞ ለወደፊት ለሚወስናቸው ህዝበ ውሳኔዎች የራሱ የሆነ አሉታዊ ጫና ያሳድሩበታል። ይህን ግንዛቤ ግምት ውስጥ በማስገባት የፖለቲካ አካሄድን ማስተካከል የትግራይን ፖለቲካ ከያዙት አካላት ይጠበቃል። የትግራይ ገዢ ድርጅት ማወቅ ያለበት ፖለቲካ የተቸነከረ የሃውልት ድንጋይ አይደለም በየጊዜው የሚታይና የሚሻሻል ነው። ይህ ሲሆን ህይወት ይኖረዋል። ስለሆነም ድርጅቱ የትግራይን ሁኔታ ከራሱ ፍላጎትና ርዕዮተአለም ብቻ ሳይሆን አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ማጣጣም ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን በድሮ በሬ ያረሰ የለምና “ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ” የሚለውን ቢሂል ማስታወስ ያስፈልጋል።

## ማጠቃለያ

የትግራይ መንግስት ከሁኔታዎች ጋር ራሱን የማያስተካከል ከሆነ የትግራይ ህዝብ ገዜ በገፋ ቁጥር የመገንጠል ፖለቲካ ከማሰብ ይልቅ ግላዊ ፍላጎቱን ወደሚሟላቱ እንቅስቃሴ ሊገባ ይችላል። ፍራቻዬ ይህ ይሆናል በሚል ብቻ ሳይወሰን መገንጠል የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የህዝብ ጥያቄና ተሳትፎ ያለው ሳይሆን የተወሰኑ ከችግር የራቁ ፖለቲካውን በሚያሳልጡ ውስን ቡድኖች ፍላጎት ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዳይሆን ነው። ለእኔ መገንጠል በራሱ ህዝብ ደረሰብኝ የሚለውን ሁለንተናዊ መድሎ ወይንም ጭቆና በራሱ የመጨረሻ መፍትሄ ያስገኝለታል የሚል እምነት የለኝም። ይህን ሊያስቀር የሚችለው ለመገንጠል የሚከፈለው መስዋዕትነት የሰው ልጅን ነጻ ማውጣት ወደሚችለው የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባት መሸጋገር ቢችል ነበር። ምክንያቱም የዲሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብ በሰው ልጅ አዕምሮ ከሰረፀ ጭቆና አድሎ በደል የሚባሉትን የአገዛዝ ደዌ እስከ ሰንኮፉ ነቅለው ይጥሉታልና ነው። መገንጠል ከብሄራዊ ጭቆና ነፃ ያወጣል ቢባል ኖሮ ኤርትራ ከሶስት አስርት አመታት፤ ደቡብ ሱዳን ከሁለት አስርት አመታት በላይ ነፃ ሀገር መስርተው ለህዝባቸው ምን ሰርተው ምን አመጡለት? ተርቦ አባሉት? ታርዞ አለበሱት? ሰላም አመጡለት? ውድ ህይውቱን በሰልጣን ወንበር ላይ ለተቆናጠጡት ጣዖቶች በከንቱ ከመገበር አዳኑት?

ከላይ እንደጠቀስኩት የትግራይ ህዝብ ላይ መንግስቴ ነው በሚለው የአዲስ አበባው ስብስብ የሰው ልጅ በዚህ ዘመን ሊሸከመው የማይችለው ግፍና በደል ተፈፅሞበታል። ይህም አልበቃ ብሎት አብይ አህመድ የውጭ መንግስታትን ጋብዞ ቀጥሮ የትግራይ ህዝብ እንዲጨፈጨፍ ንብረቱ እንዲዘረፍና ሴቶቹ እንዲደፈሩ አስደርጓል። ይህ ግፍ የትግራይ ህዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የነበረውን ሁለንተናዊ ግንኙነት በእጅጉ ጎድቶታል። ይህ ማለት ግን የትግራይ ህዝብን ጉዳት የነሱ ጉዳት አድርገው የሚቆጥሩ ውሱን ኢትዮጵያውያን የሉም ማለት አይደለም። መታወቅ ያለበት አብይና ስብስቡ የትግራይን ህዝብ ቢቻል አጥፍተውና አደህይተው መግዛት ካልሆነ ትግራይን ከኢትዮጵያ አስወጥተው ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ማምጣትና ኤርትራ የግላችን ኢትዮጵያ የሁላችን በሚል ፈሊጥ የኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ኤርትራ ፍፁም አምባገነንነት ውስጥ አስገብቶ መግዛት ነው። አብይና ኢሳያስ ይህን ወንጀል በትብብር እየፈፀሙት መሆኑን አለም ያውቀዋል። ሆኖም ግን አንዳንዴ ወንጀል ፈፃሚ እውነተኛ ዳኛ ካላገኘ ወንጀለኛው ነጻ ወጥቶ ተበዳዩ የወንጀለኛውን ቦታ ተክቶ የተዛባ ፍርድ የሚገኝበት ኢጋጣሚዎች አሉ።

በመጨረሻም ይህች አለም ጨካኝና ጉልበተኞች የፈለጉትን የሚያደርጉበት ጉደኛ ምድር ናት። ግለሰቦች፤ ቡድኖችና ሀገራት ከሞራልና ከሰባዊነት ባፈነገጠ ቁሳዊ ፍላጎታቸውን በማንኛውም መልኩ ለማግኘት ፉክክር ውስጥ የገቡበት ጊዜ ላይ ነው የምንገኘው። ማወቅ ያለብን በዚህ የዲጂታል ዘመን ግልጽ በሆነ መልኩ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መንግስታትና ተባባሪዎቻቸው በትግራይ ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈጽሙ አቅማቸውን ተማምናው ሳይሆን ከሃያላን ሀገራት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ይሁንታን ስውር እገዛ በማግኘታቸው ነው።

እነዚህ የደሃ ደሃ ሁለት አገሮች ያለውጭ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ለሁለት አመት ቀርቶ ለአንድ ወር ይህን የመሰለ ጦርነት ማካሄድ አይችሉም። ይህ ግምት ውስጥ ሳይገባ በአንዳንድ የትግራይ ተወላጆች እየተስተጋባ ያለው ግልጽ የመገንጠል ጥያቄ ተፅእኖ ፈጣሪ በሆኑ ኃያላን መንግስታትና የነሱ ጉዳይ አስፈፃሚ በሆኑ አለም አቀፍ ተቋማት ይሁንታና ድጋፍ ካላገኘ ነገሩ ጉንጭ አልፋ ነው የሚሆነው። በይበልጥም  ባለንበት ቀጣና ያለው እጅግ የተለየ ቋንቋ፡ባህል፡ ኃይማኖት የተሰበጣጠረ የህዝብ አሰፋፈርና ፍላጎት ውሱን የተፈጥሮ ሃብትና የተዛባ አጠቃቀም ግምት ውስጥ ሲገባ መገንጠል ለሃያላን ሃገራት የራስ ምታት ነው የሚሆንባቸው። ስለዚህ የመገንጠል ሃሳብን ለማክሰም የማታ ማታ ኃያላን መንግስታት ጉልበተኛውን ወገን ደግፈው ጥያቄውን ሊያዳፍኑት ይችላሉ። ታዲያ በውጤቱ ትግራይ ምን ትጠቅማለች? የወደፊቱ እጣፈንታዋስ ምን ላይ ይመሰረታል? መልሱን ለአንባብያን ትቸዋለሁ።

**ሰላምና ጤና በጦርነትና በሰው ሰራሽ ረሃብና እርዛት ለሚሰቃየው የሃገሬ ህዝብ!!!**